

## የIEC መርሃ ግብሮች በትምህርት ቤት ውስጥ ባሉት ድርጊቶች ላይ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ በሙሉ ተሳትፎ እንዲያደርግ አንድነትን ለማበረታታት ይሆናል።

| ትምህርት ቤቶች | አድራሻ | ለማነጋገር |
|---|---|---|
| አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች (ከክፍል/Years 1 እስከ 6) | | |
| /Atwell አንደኛ ደረጃ ትምሀርት ቤት* | 160 Lydon Boulevard, Atwell 6164 | 6174 2400 |
| ቢኮንስፊልድ/Beaconsfield አንደኛ ደረጃ ትምሀርት ቤት | 5 Hale Street, Beaconsfield 6162 | 9432 1000 |
| ዲያነላ/Dianella የመጀመሪያ ኮሌጅ | Laythorne Street, Dianella 6059 | 9263 5100 |
| ኢድይስቶን/Eddystone አንደኛ ደረጃ ትምሀርት ቤት* | Littorina Avenue, Heathridge 6027 | 9406 5100 |
| /Ellenbrook አንደኛ ደረጃ ትምሀርት ቤት | 65 Fortescue Place, Ellenbrook 6069 | 9297 7300 |
| ሃይጌት/Highgate አንደኛ ደረጃ ትምሀርት ቤት | 147 Lincoln Street, Highgate 6003 | 9253 2700 |
| ኮብዶላ/Koondoola አንደኛ ደረጃ ትምሀርት ቤት* | 50 Burbridge Avenue, Koondoola 6064 | 9345 6200 |
| ኖላማራ/Nollamara አንደኛ ደረጃ ትምሀርት ቤት* | 101 Harrison Street, Nollamara 6061 | 9413 1550 |
| ፓርክዉድ/Parkwood አንደኛ ደረጃ ትምሀርት ቤት* | Zelkova Way, Parkwood 6147 | 9235 1411 |
| ቶርንሊ/Thornlie አንደኛ ደረጃ ትምሀርት ቤት | 86 Thornlie Avenue, Thornlie 6108 | 9232 3480 |
| ከፍተኛ ደረጃ ትምሀርት ቤቶች (ከክፍል/Years 7 እስከ 10) | | |
| በልጋ/Balga ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 2 Markham Way, Balga 6061 | 9247 0219 |
| ግሪንዉድ/ Greenwood ኮለጅ | Coolibah Drive, Greenwood 6024 | 9243 9200 |
| ልይንዉድ/Lynwood ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 436 Metcalf Road, Parkwood 6147 | 9354 0600 |
| መልቪል/Melville ከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 18 Potts Street, Melville 6156 | 6274 1300 |
| ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶቶች (ክፍል/Years 11 እና 12) | | |
| ስይሪል ላክሶን ከፍተኛ ካምፓስ/Cyril Jackson Senior Campus | 53 Reid Street, Bassendean 6054 | 9413 4720 |
| ኖርዝ ለይክ ከፍተኛ ካምፓስ/North Lake Senior Campus | 188 Winterfold Road, Kardinya 6163 | 9314 0444 |

* እነዚህ ትምህርት ቤቶች በሰብአዊነት ወይም በትምህርታቸው ውስንነት ለለባቸዉ ተማሪዎች በአሁኑ ጊዜ የቅድመ አንደኛ ደረጃ መርሃ ግብሮችን ያካሂዳሉ።

Amharic

Department of Education
GOVERNMENT OF WESTERN AUSTRALIA

# የጥልቀት እንግሊዝኛ ማእከላት

## ለአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች


CC BY



# በጥልቀት እንግሊዝኛ መማሪያ ማእከላት ምንድ ናቸው?

**በቅርቡ ወደ ዌስተርን አውስትራሊያ ለመጡ ተማሪዎችና በምንግሥት ትምህርት ቤት መመዝገብ ለሚፈቀድላቸው ተማሪዎች በጥልቀት እንግሊዝኛ የመማሪያ ማእከላት (IECs) በኩል ለየት ባለ ሙያ እንግሊዝኛ እንደ ተጨማሪ ቋንቋ ወይም አነጋገር ዘይቤ (EALD) ትምህርት የሚሰጥበት ይሆናል።**

የ IEC ተማሪዎች ከተለያዩ ብዝሓነት ቋንቋዎችና ባህሎች ካለባቸው አገሮች የመጡ ሲሆን ታዲያ ሁሉንም ያካተተ አስደሳች የትምህርት ቤቱ አካባቢ ለመፍጠር አስተዋጽኦ ያደርጋል። በIEC እስከ 12 ወራት (ወይም ተማሪው የሰብዓዊነት ቪዛ ከያዘ እስከ 24 ወራት) መሳተፍ እንደ የተማሪው ቪዛ እና ፍላጎት ይወሰናል።

የጥልቀት እንግሊዝኛ የመማሪያ ማእከላት (IECs) የሚገኙት በዋና ትምህርት ቤቶች ውስጥ ነው። በፐርዝ ከተማ ክልል ውስጥ የህዝባዊ ትምህርት ቤቶች ላይ አስራ አራት ማእከላት እንዳሉ - ስምንቱ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ፤ አራቱ ደግሞ በሁለተኛ ደረጃ/ high ትምህርት ቤት ውስጥ እንዲሁም ሁለቱ በከፍተኛ ደረጃ/ senior ትምህርት ቤት ካምፓሶች ውስጥ ይገኛሉ።

በትምህርት ቤት ባሉ ድርጊቶች ሁሉ በመሳተፍ፤ ይህም ለትምህርታዊ እረፍትና ሽርሽር፤ ስፖርት ጨዋታ፤ ማሕበራዊ ድርጊቶች እና ስብሰባዎችን ያካተተ ለማካሄድ ከትምህርት ቤት ማህበረሰብ ጋር እንዲገናኝ የ IEC ፕሮግራሞች ያበረታታሉ።

አንደኛ ደረጃ IECs ዕድሜያቸው ከ5–11 ለሆኑ ተማሪዎች ያስተናግዳል፣ ሶስት የአንደኛ ደረጃ ማእከላት የጀርባ ታሪካቸው በሰብኣዊነት ከመጡ ዕድሜያቸው 4 ዓመት ለሆኑ ተማሪዎች የመለማመጃ ክፍለትምህርት ይሰጣል። የሁለተኛ ደረጃ IECs ማእከላት/ እድሜያቸው ከ 12* እስከ 16 ዓመት ለሆኑ ተማሪዎች ያስተናግዳል። ከፍተኛ ደረጃ IECs ማእከላት እድሜያቸው 16 ዓመት እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ተማሪዎች ያስተናግዳሉ።

*የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ 7ኛ ክፍል የሚጀምሩ ተማሪዎች በዚያ ዓመት ከሐምሌ ወር በፊት ዕድመያቸው 11 ዓመት ወደ 12 እየገቡ ሊሆኑ ይችላሉ።

## የማእከሉ/IEC ጥቅም

- ለየት ያለ በጥልቀት የእንግሊዝኛ ቋንቋ ማስተማርያ ድጋፎችና መመሪያዎች የተማሪዎቹን ዋናው ስርዓተ ትምህርት የማግኘት ችሎታ ከፍተኛ እንዲሆን ማድረግ
- በግለሰብ ደረጃ ማስተማርን የሚደግፉ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው የክፍል መጠኖች
- ባህላዊ ድጋፍ በኣንድ ጥሩ እንክብካቤ ያለበት ቦታ
- ለየት ያለ ሙያ ያላቸው አስተማሪዎችና የድጋፍ ሰራተኞች።
- በአንደኛ ደረጃ እድሜ ላሉ ህጻናት በየቀኑ ያለክፍያ በነጻ የአውቶቡስ አገልግሎት።
- ለየት ላሉ የጤና ጥበቃ አገልግሎቶችን ለመጠቀም።

## በማእከሉ/IEC ላይ ስርዓተ ትምህርት

በጥልቀት እንግሊዝኛ ማእከላት በኩል እንደ ዌስት አውስትራሊያ ስርዓተ ትምህርት መሰረት ከተማሪዎቹ ሁኔታ የሚሄዱ የተለያዩ መማሪያ መርሃ ግብሮችን ያቀርባል።

በማእከሉ/IEC ውስጥ ያለው የስርዓተ ትምህርት ዓላማ ያደረገው በእያንዳንዱ ተማሪ የሚያስፈልገው የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ይሆናል። ተማሪዎችን ያለ ምንም ችግር ወደ ዋናው የትምህርት ክፍሎች ለማሸጋገር፤ ዋና የትምህርት ዓይነቶች ሂሳብ፤ ሳይንስ፤ ሰብዓዊነት እና ማሕበራዊ ሳይንስን ያካትታሉ.

ማእከሎቹ/IECs ለተማሪዎች እንግሊዝኛ እንዲማሩ እንደሚረዱና በዌስት አውስትራሊያ ውስጥ ባሉት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በእድሜያቸው ትክክለኛ የሆነ የአካዳሚ ትምህርት እና ማሕበራዊ ይዘት እንዲያውቁ ይደረጋል። ማእከላት/IECs እና የአካባቢ ትምህርት ቤቶች አብረው የሚሠሩት ወደ አካባቢያቸው ትምህርት ቤት በቀስታ ስለመሸጋገራቸው ለማረጋገጥ ነው።

## የማእከሉ/IEC ሰራተኞች

IECs የሚቀጥረው የEALD አስተማሪዎችና ሌላ ዝርያ ያላቸው የትምህርት ረዳቶች (EEAs) ነው። EALD አስተማሪዎች ልምድ ያላቸውና በዌስት አውስትራሊያ ስርዓተ ትምህርት ጋር በተመጣጠነ መልኩ ትክክለኛ በሆነ እድሜ፤ በከፍተኛ የተቀናጀ EALD መርሃ ግብሮችን ለማቅረብ ልምዱና ሙያ አላቸው። EEAs የተለያዩ ቋንቋዎችን እንደሚናገሩ፤ ይህም የIEC ተማሪዎችን የመጀመሪያ ቋንቋ ሊያካትት ይችላል።

## በ IEC ውስጥ መጠቀም

በማእከሉ/IEC መመዝገብ የሚፈቀደው እንደ አስፈላጊነቱ እንደሆነና ከዚህ በታች ያሉትን ሊያካትት ይችላል:

- ከክፍል/Years 1 እስከ 12 ያሉት ተማሪዎች ለእንግሊዝኛ መማር አዲስ ከሆኑ፤ ይህም በአውስትራሊያ ውስጥ ለተወለዱት ያካተተ ይሆናል;
- የሰብዓዊነት ቪዛ ያላቸው ተማሪዎችና ከቅድመ-አንደኛ ደረጃ እስከ ክፍል/Year 12 ለሆኑ; እና
- ከ 6 ወራት ጊዜ በላይ ውጭ አገር ቆይታ በኋላ ወደ አውስትራሊያ ለተመለሱ ተማሪዎች .

## በማእከሉ/IEC ውስጥ ስለመመዝገብ

- ቀጠሮ ለማቀናጀት ለአካባቢዎ የ IEC ማነጋገር። (በአቅራቢያዎ ያለን ማእከል ለማግኘት በዝርዝር IECs ምዝገባ ላይ ማየት)
- የሚከተለው መረጃ ለምዝገባ ያስፈልጋል:
  - አውስትራሊያ ውስጥ የገቡበት ቀን;
  - የተማሪ ስም;
  - ወቅታዊ አድራሻ;
  - በቤት ውስጥ የሚነገሩ ቋንቋዎች/የአነጋገር ዘይቤዎች;
  - የቪዛ ንኡስ ምድብ ቁጥር; እና
  - ለማነጋገር ዝርዝር አድራሻ።
- የመመዝገብ ሂደቱን ለመደገፍ፤ ወደ IEC ለመሄድና ከዚያ ለመጣት የሚረዳ ትራንስፖርትና የአስተርጓሚ አገልግሎት ያለ ክፍያ በነጻ ይቀርባል።

